የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDRAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ—ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 32
ADDIS ABABA-4th July, 2002


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፬/፲፱፻፺፬ ዓ.ም
የኢትዮ—ጅቡቲ ፣ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ...... ገጽ ፩ሺ፰፻፴


## CONTENTS


Proclamation No. 284/2002
Ethio-Djibouti Utilization of Port of Djibouti and Services to Cargo in Transit Agreement Ratification Proclamation ................................................ Page 1830


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፬/፲፱፻፺፬

### የኢትዮ—ጅቡቲ ፣ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ· እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት ሚያዝያ ፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. በጅቡቲ ላይ የተፈረመ ስለሆነ ፤

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ተዋዋይ ሀገሮች በየሕጎቻቸው መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን አንዱ ለሌላው ሲያሳውቅ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተገለጸ በመሆኑ ፤

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ስምምነቱን ያፀደቀው በመሆኑ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ አዋጅ "የኢትዮ—ጅቡቲ፣ የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፬/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጅቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ሚያዝያ ፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም. በጅቡቲ የተፈረመው የጅቡቲ ወደብ አጠቃቀምና በትራንዚት ላይ ያለ ጭነት አገልግሎት ስምምነት ፀድቋል ።

### *PROCLAMATION NO. 284/2002*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO–DJIBOUTI AGREEMENT ON THE UTILIZATION OF PORT OF DJIBOUTI AND SERVICES TO CARGO IN TRANSIT*

WHEREAS, an Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti, on the Utilization of the Port of Djibouti and Services to Cargo in Transit, was signed in Djibouti on the 13th day of April, 2002;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force when both contracting parties have notified each other that their legal requirements for the entry into force of the Agreement have been fulfilled;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives has ratified said Agreement at its session held on the 4th day of July, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby Proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Ethio-Djibouti Utilization of Port of Djibouti and Services to Cargo in Transit Agreement Ratification Proclamation No. 284/2002."

2. *Ratification of the Agreement*
The Ethio-Djibouti Agreement on the Utilization of Port of Djibouti and Services to Cargo in Transit signed in Djibouti on the 13th day of April, 2002, is ratified.

፫· <u>ስለአስፈጻሚ አካላት ሥልጣን</u>

መንግሥት የሚወከላቸው አስፈጻሚ አካላት፣ በየሥራ መስካቸው ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቷቸዋል ።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም·

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



3. *Powers of Ececutive Organs*

The executive organs to be delegated by the Government are hereby empowered to implement the Agreement with regard to their respective fields of activity.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 4th day of July, 2002.

Done at Addis Ababa, on the 4th day of July, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE